# ባይ ባይ ሰለሞን ተካልኝ

**„የማታውቅበትን የስው ግምጃ ለብሳ**
**ተመልሺም ቢሎአት ወዴት ተመልሳ“።**

ለሰለሞን ተካልኝ ልለው የምችለው ይህንን ነው ።

የሀገር ፍቅር ራዲዬ የወያኔ ሆኖ በሰሜን አሜሪካ የሚተላለፍ ሲሆን እሁድ 30.04.2007 የዘፋኙን የሰለሞን ተካልኝን የፓለቲካ አቋም መቀየር የሚያበስረውን ቃለ መጠይቅ አቅርቦልናል።

የዘፋኙ ሰለሞን ወደ ወያኔ መመለስ ወያኔ ታላቅ ድል እንዳደረገ የቆጠረበት ቀን መሆኑን የምናውቀው በተለያዩ የወያኔ ሚድያዎች የሰለሞን ተካልኝ እጅ መስጠት እንደ ታላቅ በአል ተቆጥሮ ምድረ ወያኔ ተሰብስቦ ጮቤ ሲረግጥ በማምሸቱ ነው። ሰለሞን ለአሰር አመት የተከተለው ትግል በግል ጥቅም እንዳላገኘበትና እሱንም ጥርስ እንደሌለው አንበሳ ስላደረገው፣ በግል ክብርና ሞገሱ እንዳይረሳበት፣ ወያኔ በግል ለእርሱ በሰጠው የመደራጀት፣ የመናገር መብትን በመጠቀም በግል የደረሰበትን የፖለቲካ ክስርት ለመመለስ ጥረት መጀመሩን አውጆአል።

ሰለሞን በኤርትራ ዘመድ አዝማድ እንደሌለው ብቸኝነት እንዳጠቃው ገልፆ በገንዘብ ተግዝቶ ሳይሆን  ኢትዮጵያን ለማዳን ወደ ኤርትራ እንደተጓዘና  አሁንም እንደ በፊቱ በኤርትራ የተመሰረተውን ህብረት ተቃውሞአል። በዚህም አስታኮ ቅንጅትን ወንጅሎአል። የወያኔ ሬድዮ አዘጋጆች የሰለሞንን ፀባይ በሚገባ ስለሚያውቁት በመጀመሪያ የእሱን ትልቅነት ነግረውት የሚፈልጉትን እንዲልላቸው አድርገውታል። ወደ ወያኔ መመለሱን የፖለቲካ ብስለት ነው ብለው አድንቀውለታል። በተለይ ወያኔን የሚቃወሙ ታዋቂ ሙዚቀኞችን እንዲሰድብ ቀስቅሰውታል። ሰለሞን በአርቲስቶቹ ላይ በወያኔ የደረሰውን ጭቆና እረስቶ በተቻለው መጠን ወቀሳውን አሰምቶአል።

ሰለሞን የሬድዮኑ አባላት እንዳሉት የጥላቻ አጋንንቱ በወያኔ የፍቅር ጠበል ተጠምቋል። ሰለሞን እያደር ጠበሉ ሲሰራ ምን ጉድ እንደሚያመጣ ባላውቅም ገና መጀመሩ እንጂ ማለቂ እንዳልሆነ መገመት ይቻላል። ለግዜው ግን ሰለሞን ጦርነቱን የጀመረው አርቲስት የሆኑትን በመውቀስ ነው። ሁሉም ዜሮ ዜሮ ማለት ይህ ነው።

ስለሰሞን ወያኔዎች ብዙ እንዳልሰደቡት ሁሉ አሁን ደግሞ እኛ  ዘላለማዊ ጠላት የለንም ማንም ሰው በወያኔ ጠበል እስከተጠመቀ ድረስ ወዳጃችን ነው ብለው የሰለሞንን አርቆ አሳቢነት ታላቅ አርቲስትነት ነግረውናል። ሰለሞን በተጠመቀበት ቀን በዚያው ራዲዮ በተደረገው ትምህርት የዴያስፖራ ፖለቲከኛ ሁሉ በተለይም ኢሕአፓን ሲሰድቡ ነበር ። ይህ የወያኔ የዘር ፖለቲካ ቁስ ሰለሞንን በማጥመቁ የጳጳስነት ሹመት ከወያኔ ቢያገኝ ሰለሞንም ወደ ቀስና ከፍ ቢል አይገርመኝም አይደንቀኝም።

ሰለሞን ለዚህ በጥላቻ ጠበል ስዎችን በገንዘብ  ለሚያጠምቅ ራድዮ ከዛም ለወያኔ ማደሩ ምክንያት በፓለቲካ እየበሰለ መምጣቱን ነው የገለፀልን። ከቴም መብሰል። እኔ በበኩሌ ይህንን ይበልጥ መደናግር ነው የምለው። ሰለሞን ለሚሌኒየም የተሸጠ ይመስለኛል። የታሰሩትን መሪዎች እንዲሁም ኢሕአፓን እንደጠላት ፈርጆ በወያኔ የሚተዳደረው ራዲዮ ሰለሞን ቃለመጠይቅ ለመስጠት ሲሰማማ ድሮ በወያኔ

የተገደሉትና ፕሮፌሰር አስራትን መካዱ መሆኑን አጥቶት ነው? በቅርብ የተገደሉትን ወጣቶች አይን ሳይፈርስ እነርሱ መክዳቱ ምን ያህል የሞራል ዝቅጠት ላይ መገኘቱን ያሳየናል። ከአሁኑ የሚገርመኝ ግን በቅርብ ወያኔ ተጠቅሞ እንደሚጥለው ነው።የዛን ግዜ የኢትዮጵያን ህዝብ አይን ማየት እንደማይችል ነው። ሰለሞን በየሳምንቱ አቋሙ ይለዋወጣል እና አኛም አብረን አንታመስም። ሰለሞን በየሳምንቱ የትግሉን ስልት ይለውጣልና የኢትዮጲያ ህዝብ አብሮ ሲቀያይር አይውልም። የኢትዮጵያውያን አንዴም ለሁሌም ለወያኔ ያለውን ጥላቻውን በግንቦቱ ምርጫ አሳይቶአል። የሰለሞን በግለሰብ ደረጃ ወደ ወያኔ መመለስ የሚፈይድው ከግል ጥቅም ባሻገር ምንም የለም።

ሰለሞን ይህንን የሰላማዊ ትግል ጬኸቱን በተቃዋሚዎች ሚዲያ ለመጠቀም አለመፈለጉ ምን ያህል ከወያኔ መጠጋቱን ያሳያል። ሰለሞን ብሎ ብሎ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ይበቃናል ብሎአል። ይህን ነው የንቃተ ህሊና መመንጠቅ። አንዱ ፓርቲ ወያኔ ይሆን? ወሬ ሲዳራ እራስን መወንጀል ይጀመራል። ሰለሞን አዲስ አባባ ሄዶ ወያኔ በሰጠው የመደራጀት መብት ተደራጅቶ ታግሎ ሊያታግለን ቃል ገብቶልናል። ለቅንጅት መሪዎች የተከለከለውን መብት ፣ ለኢህአፓ እንዲያውም ያልተፈቀደለት መብት ለእሱ በግሉ ስለተሰጠው እሱም መብቱ እንዳለ አድርጎ ሲያቀርብ ምን ይሰማዋል ብዬ መገመት ያዳግተኛል። ለዚህም ነው ባይ ባይ ሰለሞን ነው ያልኩት።

ሰለሞን ግለሰብ ነው ብለን ብዙም ስለማይጠበቅበት ልንተወው ይገባል ብላችሁ የምትሉ አትጠፉም እኔም የአንድ ሰሞን ወሬ እንጂ ሌላ አይሆንም ብዬ ለሰለሞን ጉድ አንድ ሰሞን ነው የሚለውን ዘፈን በመመረጥ የሚቀጥለውን ቃለመጠይቁን ሰምተን በጣም ከበሰለው ንቃተ ህሊናው ያገኘሁትን በሚቀጥለው አቀርባለሁ ።

በልጅግ አሊ

- ቃለ መጠይቁን ለመስማት ለምፈልጉ!!!!

http://www.hagerfikerradio.com/4292007/mp3player.html